

# ፍርደ-ገምድል ዳኛ!

እልኻም ሰበበኛ
በር አቁሞ ዘበኛ
የሚያጋጥም ጠበኛ
ሳይገሰግስ እግረኛው
ይላክበት ደመኛው።

በድኻ መከረኛ
ሲፎክር ጥጋበኛ
ቢጋልብ ፈረሰኛ
ይዘፍናል ዓለመኛው
መዲና ዘለሰኛው…

ኣፈር ይብላ ያ ዳኛ
ፍርደ-ገምድል ግፈኛ፣
ጉረኛ፣ ትዕቢተኛ፣
በልቶ አይጠግብ ጉቦኛው
ያውርድበት መጋኛው!

ዳኛው እጅግ ሲከፋ
አጉል ድካም! አትልፋ
በከንቱ እንዳትጠፋ፤
የዳኛ ፍርደ-ገምድል
ሰውን በቁም ይገድል…

ገ/ኢ. ጎርፉ።